በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

# የህግ የበላይነት በዴሞክራሲ ሽግግር ሂደት

የሰው ልጅ ከሌሎች ፍጡራን የሚለይበት አይነተኛው ምክንያት ክፉ እና ደጉን፣ ጠቃሚና ጎጅውን ለይቶ ለማወቅ የሚያስችል አዕምሮአዊ አቅም እና መሰረታዊ ነጻነቶችን በተፈጥሮው የተቀደጀ መሆኑ ነው። በዚህም የተነሳ ነው የሰው ልጅ ክፉም ይሁኑ ደግ፣ ጠቃሚም ይሁኑ ጎጅ ድርጊቶቹን በራሱ ፈቃድ አስቦ ማድረግ እንዲሁም በነጻ ፈቃዱ ይሆነኛል፣ ይበጀኛል ያለውን መንገድ፣ ህይወት፣ ኑሮ፣ ሙያ ወዘተ መምረጥ የሚያስችል ችሎታ ባለቤት ነው የሚባለው። በመንግስት በሚተዳደር የፖለቲካ ማህበረሰብ ውስጥ ሀይልን በብቸኝነት የመጠቀም ስልጣን (monopoly of violence) የመንግስት በመሆኑ ደካማውም (powerless) ሆነ ጠንካራው (powerful) በመንግስት ሃይል ጥበቃ ከደህንነት ስጋት ነጻ ሆነው ተፈጥሮአዊ አቅማቸው እና ችሎታቸው የፈቀደላቸውን ያህል የህይወት ግባቸውን እያሳኩ የሚኖሩበት ሁኔታ ይፈጠራል ተብሎ ይታመናል። መንግስት የፖለቲካ ማህበረሰብ አባላቱን ከደህንነት ስጋት ነጻ ሆነው የሚኖሩበትን ሁኔታ የሚፈጥረውም ህግ እና ስርዓት በማስፈን ነው። መንግስት ህግና ስርዓት ለማስፈን ህግ ያወጣል፣ ያወጣውንም ህግ በፍርድ ሃይል እንዲሁም እንደ ህግ አስፈጻሚነቱ ሃይልን በብቸኝነት የመጠቀም ስልጣኑን ተጥቅሞ ያስከብራል። ይህን ሁኔታ/ሂደት በተለምዶ የህግ የበላይነት (supremacy of the law) ማስከበር በመባል የሚታወቀው ነው።

መንግስት የህግ የበላይነት የሚያስከብርበት አግባብ እና ሁኔታ እንደ የባህርይው እና እንደየሚከተለው የፖለቲካ ሁኔታ ይለያያል። ጠቅለል አድርጎ ለማስቀመጥ መንግስት የህግ የበላይነትን የሚስከበርበት አግባብ እና ስርዓት ከ "በህግ መግዛት" (rule by law) እና "የህግ ገዥነት"/ "በህግ መተዳደር" (rule of law) የፖለቲካ ሁኔታ አንጻር ማየት ይቻላል።

***በህግ መግዛት (rule by law)***

*አምባገነን መንግስት ወይም ጨቋኝ ስርዓት በነገሰበት ሀገር የህግ እና የፍትህ ተቋማት ምንም እንኳን ተፈጥሮአዊ ተግባራቸው የሆነውን ህግና ስርዓት ለማስፈን የሚያገለገሉ ቢሆንም ቅሉ በመሰረታዊነት ግን ዜጎችን አፍኖ እና ጨቁኖ ለመግዛትና የገዥዎቸን ጥቅምና እና ፍላጎት በተለይ ስልጣንን ለማስጠበቅ ይውላሉ። በሌላ አገላለጽ ህግና የፍትህ ተቋማት የገዥዎች የአገዛዝ መሳሪያ ሆነው ያገለግላሉ። ይህ አይነቱ ፖለቲካዊ ሁኔታ* (ስርዓት) በህግ መግዛት (rule by law) የሚባለው ነው። በህግ መግዛት የፖለቲካ ሁኔታ የህግ የበላይነት ማስከበር ማለት የገዥዎችን ፍላጎትና፣ ጥቅም እና ሥልጣን ፍጹም በሆነ አኳኋን ሊረጋገጥበት የሚችል ህግና ስርዓት (law and order) ማስፈን ነው። ለዚህም ሲባል የገዥዎችን ጥቅምና ፍላጎት የሚያስከብሩ በአንጻሩ የዜጎችን መብት፣ ነጻነት እና ጥቅም የሚደፈጥጡ ህጎች እንዲወጡ እና እንዲተገበሩ ይደረጋል። የዳኝነት አካሉ የዜጎች መብት፣ ነጻነት እና ጥቅም የሚጥሱ ህጎችን በህግ የበላይነት ማስከበር ሽፋን በተግባር ላይ እንዲውሉ ያደረጋል። የህግ አስፈጻሚው አካልም ህግና ስርዓት (law and order) በማስፈን ሽፋን የዜጎችን በህይወት የመኖር እና የአካል ደህንነት መብት፣ የመንቀሳቀስ ነጻነት እንዲሁም ሌሎች መሰረታዊ መብቶችና ነጻነቶችን በሚጥስ አኳኋን የመንግስትን በብቸኝነት ሃይል የመጠቀም ስልጣን (monopoly of violence) በመጠቀም አፋኝ፣ ጨቋኝና ኢፍትሃዊ የሆኑ ህጎችን ሳይሸራረፉ እንዲተገበሩ ያደርጋል።

**የህግ ገዥነት/ በህግ መተዳደር (rule of law)**

ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እና መንግስት ባለበት ሀገር ህግና የፍትህ ተቋማት መሰረታዊ አላማ እና ተግባር የዜጎችን መሰረታዊ ነጻነት፣ መብት፣ እኩልነት በሚያከበር እና የጋራ ጥቅም፣ ማሕበራዊ ፍትህ፣ ብልጽግና፣ ሰብአዊ ደህንነትን (human security) እና ደህንነትን በሚያረጋገጥ መልኩ ህግና ስርዓትን (law and order) ማስፈን ነው። በህግ ገዥነት/በህግ የመተዳደር የፖለቲካ ሁኔታ የህግ የበላይነት ማስከበር ማለት ገዥና ተገዥ በማይኖርበት አኳኋን መንግስትም ሆነ ዜጎች፣ ሀይለኛውም (powerful) ሆነ ደካማው (powerless) በህግ ፊት እኩል በሚታዩበት እና በሚዳኙበት አግባብ የዜጎችን ጥቅም፣ ፍላጎት ለማስጠበቅ የወጡ ህጎች የዜጎችን መሰረታዊ ነጻነቶችና መብቶች ባከበረ መንገድ በመተግበር ማህበራዊ ፍትህን፣ ብልጽግና፣ ሰብአዊ ደህንነትን እና ሰላምን ማረጋገጥ የሚችል ህግ እና ስርዓትን (law and order) የመንግስትን በብቸኝነት ሃይል የመጠቀም ስልጣን (monopoly of violence) በመጠቀም ጭምር ማስፈን ነው። ለዚህም ሲባል የሚወጡ ህጎች

የዜጎችን ፍላጎት ጥቅም የሚያስጠብቁ እና መሰረታዊ መብታቸውን እና ነጻነታቸው የሚያከበሩ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ የዳኝነት አካሉ ተፈጥሮአዊ ነጻነቱን በመጠበቅና በገለልተኛነት እነዚህን ህጎች የዜጎችን መሰረታ መብቶችና ነጻነቶች በሚያከብሩ መልኩ ይተረጉማል፣ ይተገብራል፡፡ የህግ አስፈሚው አካልም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የመንግስትን በብቸኝነት ሃይል የመጠቀም ስልጣን (monopoly of violence) በመጠቀም ጭምር፤ ሆኖም መሰረታዊ ነጻነቶች በማይጥስ መልኩ እነዚህን ህጎች የመንግስት ሹማምንት ጨምሮ በሁሉም ዘንድ እኩል እንዲከበሩና እንዲተገበሩ ያደርጋል፡፡

## የህግ የበላይነት በዴሞክራሲ ሽግግር ባለች ኢትዮጵያ

ጠቅለል ባለ መልኩ እንደተቀመጠው የህግ የበላይነት የማስከበር አግባብ እና ስርዓት በህግ መግዛት (rule by law) እና በህግ ገዥነት/ በህግ የመተዳደር የፖለቲካ ሁኔታ ውስጥ የተለያየ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የህግ የበላይነት በዴሞክራሲ ሽግግር ባለችው ኢትዮጵያ ከህግ የበላይነት አንጻር ሽግግሩ ከበህግ መግዛት (rule by law) የፖለቲካ ሁኔታ ወደ የህግ ገዥነት/በህግ መተዳደር የፖለቲካ ሁኔታ መሆኑን ልብ ሊባል ይገባል፡፡ ለባለፉት ሦስት ዓመታት በሀገራችን ተጀመረው ለውጥ ተከትሎ አዲስ የዴሞክራሲ ጉዞ ከመጀመሩ በፊት በነበረው ጊዜ የነበሩት በጎ ጎኖች እንዳሉ ሆነው በህግ መግዛት (rule by law) የፖለቲካ ሁኔታ የሚገለፅ መሆኑ ብዙም የሚያከራክር አይደለም፡፡ በዚህ ወቅት የዜጎችን መሰረታዊ መብቶችና ነጻነቶችን በተለይም ሀሳብን የመግለፅ፣ የመሰብሰብ እንዲሁም የመደራጀት መብት የሚገድቡ ህጎች ወጥተው በመተግበራቸው የዜጎች የዴሞክራሲ ተሳትፎ የቀጨጨበት እንዲሁም በአጠቃላይ የፖለቲካ ምህዳሩ በከፋ ሁኔታ የሀሳብ ብዝሃነት የማይስተናገድበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር፡፡ የዳኝነት አካሉን ጨምሮ የፍትህ ተቋማት በነጻነትና በገለልተኛነት የዜጎችን ፍላጎት እና ጥቅም በሚያስከብር ሁኔታ ግዴታቸውን መወጣት ሲገባቸው መሰረተ ቢስ ክሶችን ህገ-ወጥ በሆነ በመንገድ በማዘጋጀት እና በመዳኘት የዜጎችን መሰረታዊ መብቶችና ነጻነቶችን በማፈን ረገድ ተባባሪ ሆነው የተገኙበት ሁኔታ አልነበረም ብሎ በድፍረት ለመናገር የሚቻል አይደለም፡፡ የህግ አስፈጻሚ እና የፀጥታ አካላትም ህግ እና ስርዓት (law and order) በማስፈን ሰበብ የመንግስትን በብቸኝነት ሀይል የመጠቀም ስልጣን በመጠቀም በተለይም መንግስትን የሚቃወሙ እና የሚተቹ ዜጎችን ህይወት፣ የአካል ደህንነት እንዲሁም የመንቀሳቀስ ነጻነት ላይ ጉዳት የሚያደረሱ ተግባራትን ያለምንም ተጠያቂነት (with impunity) የሚፈጽሙበት ሁኔታም ተፈጥሮ አልነበረም ማለት አይቻልም፡፡

በአንጻሩ የአመራር ለውጡን ተከትሎ የሀገራችን የፖለቲካ ሁኔታ ከበህግ መግዛት(rule by law) ወደ የህግ ገዥነት/ በህግ መተዳደር (rule of law) የሚያሻገሩ እርምጃዎች ተወስደዋል፡፡ በተቃውሞ ፖለቲካ ተሳትፏቸው የተነሳ ታስረው የነበሩ ዜጎች ከእስር እንዲፈቱ፤ ተሰደው የነበሩ እንዲሁም በነፍጥ ትግል የጀመሩም ጭምር በነጻነት ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ ተደርገዋል፡፡ የዜጎችን መሰረታዊ መብቶች እና ነጻነቶች የሚገድቡ ህጎች መሻሻል ላይ ናቸው፡፡ የዳኝነት አካሉን ጨምሮ የፍትህ ተቋማት በነጻነት እና በገለልተኛነት እንዲሁም የህዝብ አመኔታ እና ቅቡልነትን ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ሃላፊነት እና ግዴታቸውን መወጣት ይችሉ ዘንድ መሰረታዊ ለውጥና ማሻሻያ እየተደረገባቸው ይገኛሉ፡፡ በህግ አስፈጻሚው በኩልም በተለይም የፀጥታ እና የፍትህ አካላቱ የህዝብን አመኔታ እና ቅቡልነትን በሚፈጥር እና የዜጎችን መሰረታዊ መብቶች በሚያከበር አኳኋን ህግና ስርዓትን የማስከበር ግዳጃቸውና ተልኳቸውን በውጤታማነት ማከናወን የሚስችል ብቃትና ዲሲፕሊን እንዲሁም ተቋማዊ አቅም እንዲኖራቸው ለማድረግ መሰረታዊ ማሻሻያ እየተደረገባቸው ነው፡፡ የእነዚህ የማሻሻያ እና የለውጥ እርምጃዎች የመጨረሻ አላማ እና ግብም የዜጎችን መሰረታዊ ነጻነት፣ መብት፣ እኩልነት በሚያከበር እና የጋራ ጥቅም፣ ማሕበራዊ ፍትህ፣ ብልጽግና፣ ሰብአዊ ደህንነትን እና ሰላምን በሚያረጋገጥ መልኩ የህግ የበላይነትን በማስከበር ህግና ስርዓትን ማስፈን የሚያስችል ህግ ገዥ የሆነበት ጠንካራ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት መገንባት ነው፡፡

ሆኖም በዚህ የሽግግር ወቅት ምንም እንኳን ሊጠበቅ የሚችል ቢሆንም በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች ስርዓት አልበኝነት የሚከሰትበት አጋጣሚ እየተበራከተ መጥቷል፡፡ በተለይም ከዚህ ቀደም ሆኖ በማያውቅ መልኩ እውን የሆነውን የፖለቲካ ነጻነት ለጥፋት እና ለአፍራሽ አላማ ለመጠቀም ቆርጠው በተነሱ በግጭት አትራፊ ሃይሎች እና የዴሞክራሲ ሽግግር ሂደቱን ለማጨናገፍ በሚፈልጉ ግብርአበሮቻቸው በሚያቀናብሯቸው የብሔር ማንነትን መሰረት ባደረጉ ግጭቶች የተነሳ ዜጎች ህይወታቸውን እና አካላቸውን ያጡበት እንዲሁም ቤትን ንብረታቸውን ትተው የተፈናቀሉበት ሁኔታዎች በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች ተከስተዋል፡፡

በርግጥ እንደዚህ አይነትና መሰል ሁኔታዎች በመደጋገማቸው የተነሳ መንግስት የህግ የበላይነት በማስከበር ህግና ስርዓትን ለማስፈን እየተሳነው ነው የሚል ስሜት በህዝብ ዘንድ እየተበራከተ ቢመጣ የሚገርም ምናልባትም በእነዚህ ስሜቶች በመገፋት ህግና ስርዓት ለማስፈን ሲባል መንግስት ከለውጡ በፊት ሲያደረገው በነበረው አኳኋን የህግ የበላይነትን ሊያስከብር ይገባል ሊባልም ይችል ይሆናል፡፡ ሆኖም መሰረታዊ እና ወሳኙ ጉዳይ መሆን ያለበት ይህ በእርግጠኝነት ወደ ኋላ የሚመልሰን መፍትሄ በህግ ገዥነት(rule of law) ላይ የተመሰረተ ዘላቂነት ያለው ጠንካራ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት መገንባት የሚስችለን ነው ወይ የሚለው ነው፡፡

የህግ ገዥነት ማስፈን በአጭር ጊዜ እና በቀጥታ መከናወን የሚችል ህግ-ተኮር ብቻ የሆነና የህግ ማሻሻያዎችን በማድረግ፣ የፍትህ ተቋማትን በማጠናከር እንዲሁም የህግ ተርጓሚ እና አስፈጻሚ አካላትን በማሰልጠን ብቻ የሚከናወን ቴክኒካዊ ተግባር አይደለም። ህግ ገዥ የሆነበት ጠንካራ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት መገንባት ውስብስብ እና ጊዜን የሚጠይቅ ሂደት ነው። በተጨማሪም የፖለቲካ እና ኢኮኖሚ ልሂቃኑን እንዲሁም የተራው ዜጋ ጥቅሞችን በሚነኩ ጉዳዮች ላይ በነጻነት ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ልምምድ ማድረግን የሚጠይቅ ነው። በተለይም ህግ እና ስርዓትን ሊያዳክሙ የሚችሉ የፖለቲካ እና የስልጣን ተለዋዋጭ ሁኔታዎችን ማንበር በመንግስት ሹማምንት፣ በህዝብ፣ በተለያዩ የፖለቲካ ሃይሎች እና ልሂቃኖች እንዲሁም በሲቪል ማህበረሰቡ መካከል እኩል በህግ ለመጠየቅ መተማመንን እና ስምምነት መፍጠርን ይጠይቃል። ይህን መተማመን እና ስምምነት መፍጠር ደግሞ ጊዜ እና ትግዕስት የሚጠይቅ ሂደት ነው። እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት ዋናው ጉዳይ መብት አክባሪና ለህግ ተገዥ የሆነ እንዲሁም የህግ የበላይነትን በማስከበር ህግ እና ስርዓት የማረጋገጥ የሚችል መንግስት ድንገት ሊፈጠር የማይችል መሆኑ ነው። ይህን እውን ለማድረግ የህግ ገዥነት መርሆች ማስከበር የሚያስችል እንዲሁም መንግስት ማህበራዊ እና ተቋማዊ የሆነ የህግ ገዥነት ባህል መፍጠር እንዲችል የሚያግዝ ንቁ የሆነ የህብረተሰብ ተሳትፎ እንዲኖር ያስፈልጋል።